የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካትና ሀላፊነቱን ለመወጣት አሰራሮቹ ውጤታማና ግልፅ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ የአሰራር ስርዓት መፍጠርና መተግበር አለበት፡፡

## የሙስና ምንነት

ሙስና ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ህግና ሥርዓትን በመጣስ የመንግስትና የሕዝብን ንብረት መዝረፍ፣ ማጭበርበር፣ እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በጎሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትስስር ላይ በመመርኮዝ አድሏዊ በሆነ አሰራር ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ  መጥቀም ሌላዉን በመጉዳት ከፍተኛ ጉዳትና ተጽዕኖ እያደረሰ ይጋኛል፡፡  ይህም በበጀት፣ በስራ ምዳባ፣ በውጤት ተኮር ነጥብ አሰጣጥ፣ በብሄር፣ በዝምድና፣ በፖለቲካ በወገንተኝነትና የመሰሳሉት በመጠቀም በመንግስትና በህብረተሰቡ ላይ ብዝበዛና ጭቆና ማካሄድ ነው፡፡

## የሙስና መከላከያ ስትራቴጂያዊ አላማ እና የተፈጻሚነት ወሰን

### የሙስና መከላከያ ስትራቴጂው አላማ

በተቋሙ ውስጥ አንድ ወጥ ወይም የተቀራረበ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ መቅረፅ የሚያስችል አቅም መፍጠር፣

- ✓ በተቀናጀ ሙስናን የመከላከል ስትራቴጂ ውስጥ የተቋሙ ሚና ምን እንደሆነ የማመላከት፣
- ✓ ተቋሙ ከሚጠበቅበት ተግባር እና ኃላፊነት አንጻር በባለቤትነት መንፈስ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሥራውን ለማከናወን የሚረዳውን ስትራቴጂና ዕቅድ ነድፎ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡
- ✓ በተቋሙ የሙስናና ብልሹ አሰራር ወንጀሎች እንዳይከሰቱና እንዳይስፋፉ ሙስናን የሚፀየፍ ሰራተኛ በመፍጠር የችግሩን ምንጭ ማድረቅ እና በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ከመድረሱ በፊት መቆጣጠር በሚያስችል መልኩ ለመምራት ብሎም ባለድርሻ አካላት በተቋሙ ላይ ያላቸው እምነት እንዲጎለብት ማስቻል ነው፡፡

### የስትራቴጂው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጅ በተቋሙ ባሉ መሪ ሥራ አስፈፃሚና ሥራ አስፈፃሚ እንዲሁም በክልል ከተሞች በሚገኙ ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### የመከላከያ ስትራቴጂው አጠቃላይ አቅጣጫ

ሙስናን ለመከላከልና ለመቅረፍ በሀገር ደረጃ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችንና የሕግ ማዕቀፎች ተቀርጸው ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል፤ እየተደረገም ይገኛል፡፡ በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ ላይም ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት የመልካም አስተዳደር እጦት ቁልፍ ምክንያቶች መሆናቸውን በአጽንኦት በመረዳት የፀረ-ሙስና ትግሉን በተቀናጀና በቁርጠኝነት መወጣት እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

ይህንንም አቅጣጫ በስኬታማነት ለመወጣት እና የፀረ-ሙስና ትግል በአንድ ተቋም ሩጫና ጥረት የሚቀረፍ ባለመሆኑ እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም ተቋማዊ አቅሙን አጠናክሮ እንዲሰራ የተቀየሰው አንዱ ስልት ተቋማዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራተጂ መንደፍ እና ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

ተቋሙም ይህን የሙስና መከላከል ስትራቴጂ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ አመራሩንና መላ ሠራተኛውን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በባለቤትነት ስሜት የነቃ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ የተቋሙ አመራርና ሰራተኛም የፀረ-ሙስና ትግሉን በዕውቀት ላይ ተመስርተው መንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ ስለሙስና ምንነትና ጎጅነት እና ተያያዥ ጽንሰ ኃሳቦች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፣ በተደራጀ መልኩ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን መዋጋት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር ጥረቶች ይደረጋሉ፤ ተስማሚ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት እና ስትራቴጂው አንዱ የስራ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ኃላፊ የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡

ተቋማዊ ምክንያት/ ተቋማት የተቋቋሙበትን ዋነኛ ዓላማ ከማሳካት አንፃር ባለው ወሳኝነት

- ❑ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት ለህዝብ ጥቅምና አገልግሎት የተቋቋሙ ናቸው
- ❑ የመንግሥት ተቋማት በህዝብ ሃብት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው
- ❑ የህዝብን ሁለንተናዊ ጥቅም የመጨረሻ ግብ ሊያደርጉ ይገባል

ከግዢ፣ ሽያጭና ንብረት አስተዳደር አንጻር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በውስጡ የግዢ ስርዓት መከተል ያለበትን መንገድ ሲያስቀምጥ የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር መርሆዎች በአንቀጽ 5 ስር ተዘርዝረዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ የግዢ ስርዓት አድሏዊ አሰራርን ያልተከተለ፣ ማናቸውም የግዥ ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ እና ፍትሐዊ መሆኑ የተረጋገጠ መሆን እንዳለበት ደንግጓል፡፡ የፌደራል መንግስት ተሸከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 የመሳሰሉት የመሳሰሉት መመሪያዎች ለተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ እንደ ህግ ማዕቀፎች ከሚያገለግሉት ህጎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ሀላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ሀላፊነት መመሪያ 6/2003 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህግ የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ሀላፊዎች፣ የፋይናንስ ክፍል ሀላፊዎችና የሰራተኞች የፋይናንስ ሀላፊነቶችን ደንግጓል፡፡

የወንጀል ህግ 414/96

በ1997 በወጣው የወንጀል ህግ 414/96 ሙስናን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተለይተውና ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሙስናን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለውና በቀላሉ ለማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ አንድ ላይ የተቀመጡ አልነበሩም፤ በ1997 በወጣው የተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ግን በ23 አንቀፆች አማካኝነት ድንጋጌዎቹ ተለይተው እንዲቀመጡ የተደረገ ሲሆን እነዚህም አንቀጾች በስፋት የሚታወቁ የሙስና ወንጀሎችን የተመለከቱ አንቀጾችን የያዙ ሲሆን ይህም ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነዱን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

የጸረ-ሙስናና ተያያዥ ሕጎች

1. የተሻሻለው ልዩ የሙስና ወንጀል የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ህግ 434/1997

በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ በዝርዝር የሚደነግግ ህግን እንዲሁም

በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ንብረት ስለማገድ፣ ስለማስተዳደር እና ስለመውረስ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘ አዋጅ ሲሆን ለስትራቴጂክ ዕቅዱም እንደመነሻነት ያገለግላል፡፡

2. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራር ደንብ 144/2000

ደንብ ቁጥር 144/2000 የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ነው፡፡ በደንቡ ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች መቋቋም፣ ዓላማዎች፣ ተጠሪነት፣ ተግባራት፣ የሥነምግባር ሥራ አስፈፃሚ ሀላፊነት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ሀላፊ ሃላፊነት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች ሀላፊነት፣ ቅጥር፣ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችና የኮሚሽኑ የሥራ ግንኙነት የመሳሰሉ ድንጋጌዎችን የያዘ ደንብ ነው፡፡

3. የሀብት ማሳወቂያ ማስመዝገቢያ አዋጅ 668/2002

የሀብትና ገንዘብ ጥቅሞችን ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ ሕግ በዋነኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋትና ሕዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ ለማጠናከር፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍቱ አሰራሮችን ለመዘጋት፣ የመንግስትን አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማድረግ፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የመንግስትና የግለሰብ ሀብት ተለይተው እንዲታወቁ እና በህዝብና በመንግስት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲዳብር፣ የመንግስት የስራ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሉ የሚመሩበትን ግልፅ ስርዓት ለመዘርጋትና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ እንዲሁም ህዝብ መንግስትን ይበልጥ እንዲያምንና ለመንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶች ተፈፃሚነት የላቀ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያግዝ ህግ ነው፡፡

4. የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ 699/2003

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ የወንጀል ድርጊቶች ከተፈፀሙ በኋላ ፈፃሚዎቹ ተደብቀው እንዳይቀሩና ህግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ የህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ መስጠት በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀሎችን በማጋለጥ ወንጀልን ለመከላከል፣ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎችም በምስክርነታቸው ወይም በጠቋሚነታቸው ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋና ጥቃት ለመከላከልና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የጥበቃ ሥርዓቶችን በህግ የሚደነግግ አዋጅ ነው፡፡

የሙስና መታገያ/የመዋጊያ  አጠቃላይ ስልቶች

- ጠንካራ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- ጠንካራ ድጋፍና ክትትል ማድርግ፣
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
- ተገቢ የሆኑ የአሰራር ማንዋሎች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ አሰራሮችን በመለየት ተገቢ አሰራር መዘርጋት፣

ከሙስና ስጋት ትንተና ውጤት መገንዘብ የሚቻለው የተቋሙ ዋና ዋና ተግባራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር የመጋለጥ ደረጃቸውም ሆነ የጉዳት መጠናቸው በአመዛኙ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ካላቸው የሙስና ስጋት ደረጃ አንፃርም ቅድሚያ በመስጠት እያንዳንዱን ተግባር ተገቢውን የሙስና መከላከያ ስልቶችን በመቀየስ ተፈፃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የተቋሙ የስጋት አካባቢ የሆኑ ተግባራትን ቅድሚያ በመስጠት በየደራጃ ተፈፃሚ ለማድረግ ከዚህ የሚከተሉት የሙስና መከላከያ ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

ጠንካራ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

- ይህ የሙስና መከላከል ስልት የስራ ማስፈጸሚያና መቆጣጠሪያነት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችንና የአሰራር ሥርዓቶችን (ለምሳሌ የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር፣ የብቃትና ሰው ኃብት አስተዳደር፣ የፀረ-ሙስና ሕጎችን፣ ወዘተ... የሚይዝ ነው) በማውጣት የሚፈቅዱና የሚከለክሉ ጉዳዮችንና ሥራዎችን በማመላከት የተጠያቂነትና ግልፅነት ሥርዓትን መዘርጋትና ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሥራ የሚከናወንበት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር፣ ከፀረ-ሙስና እና ከፍትህ አካላት እንዲሁም ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ መስራትን ይጠይቃል፡፡

- የውጤት ተኮር ስራ አመራርን በማዘመንን አውቶሜት በማድረግ እንዲተገበሩ ማድረግ፡፡ የክትትልና ግምገማ አግባብም ይዘረጋል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥን እንደገና በመከለስ (ሪኢንጅነር በማድረግ) የተቀላጠፈ አገልግሎትን ማረጋገጥ ሙስናን ለመከላከል ዓይነተኛ ዘዴ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ አስፈላጊውን ሎጅስቲክ በማሟላት ወደ ስራ እንዲገባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ጠንካራ ተቋማዊ ባህል በማዳበርና በማጠናከር አመራሩና ሰራተኛው የባለቤትነት ስሜቱ እንዲዳብር ማድረግ፡፡
- በተቋሙ በወጡት የአገልግሎት ደረጃዎች መሰረት ተገልጋዩ አገልግሎት የማያገኝ ከሆነ አቤት የሚልበትና ፈጣን መልስ ሊያገኝ የሚችልበት ጠንካራ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት መገንባት

ጠንካራ ድጋፍና ክትትል ማድርግ፣

- በዕቅድ አተገባበር ላይ ቅድመና ድህረ የክትትልና የግምገማ ስራዎችን ያከናውናል፣
- የግምገማውን ሪፖርት በየወሩ ለተቋሙ የስራ አመራር፣ በየሩብ አመቱ ደግሞ ለሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የማቅረብና በሚሰጥ ግብረ መልስ መሠረት አሠራሮች እንዲስተካከሉ ማድረግ፣
- የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ ስለመሆኑ መደበኛ በሆነ መልኩ አስተያየት በማሰባሰብ /ሰርቬይ በማካሄድ/ የታዩ ችግሮችንና መሻሻሎችን በመለየት ሪፖርት ማጠናቀር፣

- ለውጤታማነቱ ተገቢውን ድጋፍ፣ ክትትል እና ግምገማ ማካሄድ፣ ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፣
- ስራን መሰረት ያደረገ ግምገማ በማድረግ ቅጥርና እድገት በመፈፀም ሰራተኞች ይበረታታሉ፤ በደረጃ እድገት፣ በምደባና በዝውውር ላይ ቅሬታ ያለው ሰራተኛ ካለ በአግባቡ ቅሬታው የሚሰማበት መንገድ ይመቻቻል፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣

- ሰራተኞች በምን ዓይነት ሥነ-ምግባር ተገልጋዮቻቸውን ማስተናገድ እንዳለባቸው በየጊዜው ሥልጠና መስጠት፡
- የሙስና መከላከል እና የሥነ ምግበር ማስረጽ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎች ትኩረት መስጠት፣

የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ አሰራሮችን በመለየት ተገቢ አሰራር መዘርጋት፣

- በተቋሙ የጥቅም ግጭት ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማስወገድ ሙስናን ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ሰራተኞችም በሚሰሯቸው ስራዎች የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉትን ለይቶ በሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ ማካተት፣ ማሰልጠንና ተግባራዊነቱንም መከታተል ተገቢ ነው፡፡

የሙስና መከላከያ ስልቶች ውጤታማ ለማድረግ የሚከተሉት ተግባራት በቁርጥኝነት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡-

- ሙስናንና ብልሹ አሰራርን የማይሸከም አመራርና ሰራተኛ ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራን በተከታታይነት መስራት፣
- ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ አሰራሮች ላይ የአሠራር ስርዓት ጥናት በማካሄድ ክፍተቶችን መዝጋት፣
- የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ መረጃ ማሰባሰብ፣ መገምገምና የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- ተቋማዊ የሥነ-ምግባር ደረጃ ቅኝት ማካሄድና ውጤቱን መሰረት አድርጎ እርምጃ መውሰድ፣
- ከደንበኛና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ መስራትና የሚቀርቡ የማሻሻያ ሃሳቦችን በእቅድ አካቶ መተግበር፣
- የሙስና ጠቋሚ መረጃዎችን የማጣራት ሥራና ምርመራ እንዲካሄድባቸው ማድረግ፣
- የመልካም አስተዳደር ማስፈን ስራን አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የሥነ-ምግባር ትምህርትን የማስረጽ ሥራ በሳምንታዊና በካይዘን ልማት ቡድን ውይይቶች ወቅት አንድ የውይይት አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ ወዘተ፡፡

የበላይ ኃላፊውና የአመራሩ ኃላፊነትና ተግባር

1. በተቋሙ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የስራ መሪና ሰራተኛ እና የሰመረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ክትትል ያደርጋል፣ የተቋሙ የአሰራር ስርዓት ለሙስናና ለብልሹ አሰራ የማይመች፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ያደርጋል፣

2. በተቋሙ የሥነ-ምግባር ክፍል ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው አኳኋን በተፈላጊው የሰው ኃይልና አገልግሎቶች በማሟላትና ለኃላፊውና ለሰራኞቹ ተመጣጣኝ ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች በመስጠት ለክፍሉ ምቹ የስራ ሁኔታን ይፈጥራል፣
3. በተቋሙ ውስጥ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች፣ የሙስናና የብልሹ አሰራር ዝንባሌዎች ሲታዩ በፍጥነት ከሰራተኞችና ከስራ መሪዎች ጋር በመመካከር መፍትሄ ያፈላልጋል፣
4. የሚወሰዱ አስተዳደራዊና የዲሲፕሊን እርምጃዎች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ፣ ከቂም በቀል የጸዱ፣ በተቋሙ መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ እርምጃዎቹ ህግንና መመሪያን መሰረት ያደረጉና ፍትሃዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
5. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሰራተኛው በቂ የሥነ-ምግባር ትምህርት በየጊዜው መስጠቱን፣ ብልሹ አሰራሮችን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በበቂ ሁኔታ ተከታትሎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወድ ማድረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
6. የጠቋሚዎችን የጥበቃ ስርዓት የመዘርጋትና የጠቋሚዎችን መብቶችና ግዴታዎችን በተለይም የሚከተሉትን የሚመለከት ማስታወቂያ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ በጉልህ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡

የሠራተኛው ኃላፊነት

1. ማንኛውም የስራ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የማጋለጥ ግዴታ ያለበት መሆኑንና አለማጋለጥ የሚያስጠይቅ መሆኑን፣ ጥቆማዎች በአካል ቀርቡ በቃል ወይም በጽሁፍ፣ ስምን ገልጾ ወይም ሳይገልጽ በስልክ ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜል፣ በፋክስ ወይም በመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑን፣ በሥነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ወይም በሙስና ወንጀል ጠቋሚዎች ላይ የበቀል ዕርምጃ መውሰድ የተከለከለና ተፈጽሞ መከተገኘ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣ ሆን ብሎ ሰውን ለማጥቃት በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተቀነባበረ ጥቆማ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣
2. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የቂም በቀል እርምጃዎችን የሚመረምርና የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ መሆኑን፣ ይህንን ሲያደርግ በግልባጭ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ የሚገባው መሆኑን፣ በቂም በቀል እርምጃው ላይ ተቋሙ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰራተኛ ለኮሚሽኑ አቤቱታ ማቅረብ የሚችል መሆኑን፣ ለክትትል እንዲያመች በውጪና በውስጥ ኦዲተሮች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት የቀረበባቸው ጉዳዮችን የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ በግልባጭ እንዲያደርገው የማድረግ፣ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ለስራው ጠቃሚ የሆነ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ተገቢውን የማድረግ፣ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚፈልገውን ትብብር በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፡፡
3. ማንኛውም በተቋሙ ሰራተኛ የመስሪያ ቤቱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ሥራ አስፈፃሚ ለስራው የሚፈልጋቸውንና የሚጠይቃቸውን መረጃዎችና ሌሎች ድጋፎች በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፣
4. ትብብር ስለመከልከል በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ለሥነ ምግባር መከታተያ ሥራ አስፈፃሚ ትብብር መከልከል አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ያስከትላል ፡፡

የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ኃላፊነትና ተግባር

በልዩ ልዩ የፀረ ሙስና ህጎች በመንግስታዊ ተቋማት ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች

- የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 144/2000፣
- የኮሚሽኑ የተሻሻለው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 እና 883/2007፣
- የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97 እና 882/2007፣
- የሙስና ወንጀሎች ለመደንገግ የወጣ አዋጅ 881/2007፣
- የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 668/2002፣

እነዚህና መሰል አዋጆችና ደንቦች እያንዳንዱ ተቋም፣ የተቋሙ የበላይ ሃላፊ መላው አባላት በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ዙሪያ ሊኖራቸው የሚገባን ሚና ያመላክተዋል፡፡

እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን የሚመለከት ደንብ ቁጥር 144/2000 ፀድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ መደረጉ የሥነ-ምግባር

መከታተያ ክፍሉ በተቋሙ ለመቋቋሙ ዋንኛ ምክንያት ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ተጠሪነቱ ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር

በተቋሙ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች፣ የፀረ-ሙስና ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ የመልካም ስነ-ምግባር፣ የሙስና አስከፊ ገጽታዎችና ጎጂነት ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፣

1. የጸረ-ሙስና ፖሊሲዎች፣ የጸረ-ሙስና ህጎች፣ የተቋሙ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ስለ አፈጻጸማቸውም በተቋሙን ዋና ዳይሬክተር ያማክራል፤
2. በተቋሙን የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ አግባብነት ካላቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
3. የካውንስሉን ስራ የማስተባበር፣ የፀሀፊነት ተግባሮችን የማከናወን፣ መረጃዎች በአግባቡ መያዛቸውን ማረጋገጥ፣
4. ከሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በቅርበትና በጋራ መስራት እና ሪፖርቶችም ጊዜያቸውን ጠብቀው መደረጋቸውን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡
5. በተቋሙ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ለጥናት የሚሆኑ መነሻ ሀሳቦችን በማመንጨት ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፣ ይህንኑ የተቀመ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው ያደርጋል፣ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት አካላት ጋር በመተባበር ጥናት በማድረግ አማራጭ ሃሳቦችን ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

ግንቦት 2015 ዓ.ም.

የሥነምግባር መከታተያ ሥራ አስፈፃሚ

እናመሰግናለን!!